# ሰላምና ብሔራዊ ዕርቅ፡ ወያኔን በጠላትነት ፈርጀ በጋራ ለመታገል

በአገራችን የረዥም ጊዜ ታሪክ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍትህ እኩልነት ዲሞክራሲና ሰላም እንዲሰፍን ይህ ነው የማይባል ታላቅ መከራና ክቡር መስዋዕትነት የተከፈለበት ሰላማዊና የአመፅ እንቅስቃሴዎችን አካሂደዋል።

ካለመታደል ግን አገራችን ዛሬም ሰላም ፍትህና ዲሞክራሲ የሰፈነባት በልማትና በዕድገት ጎዳና የምትራመድ ሀገር አልሆነችም። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም እንደ ዓቢይ ምክንያት ተደርጎ የሚቀርበው የህዝብን ይሁንታን ያገኘ፡ ህዝብን በእኩልነት የሚዳኝ፡ ህዝባዊና ዲሞክራሲያዊ  የሆነ መንግሥት አለመመስረቱ፡ አገርና ህዝብ የሚተዳደሩበት ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት አለመኖሩ ነው። እስከዛሬ በተጨባጭ እንደታየው በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ የተፈራረቁበት ገዥዎቹ በየበኩላቸው አንዱ ከሌላው የሚለዩባቸው ባህርያት ቢኖራቸውም ሁሉንም ግን አንድ የሚያስመስሏቸው ባህርያትም አሏቸው። እነሱም ሁሉም በኃይል ሥልጣን መያዛቸው፡ አምባገነንነታቸው፡ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ማራመዳቸው፡ በህዝብ መካከል የጋራ መተማመንና ከበሬታን ለመፍጠር፡ ሁሉም ዘላቂ ሰላምና መረጋጋትን በሀገሪቱ ለማስፈን አለመቻላቸው ደግሞ ዛሬ ለሁሉም በግልጥ እየታየ ያለ ነው። በዚህም የተነሳ በሀገራችን ለብሔራዊ ክብርና ነፃነት፡ ለዲሞክራሲ፡ ለማህበራዊ ፍትህ፡ ለሰላምና ለእኩልነት የሚታገሉ ኃይሎች የሰላማዊ ለውጥ በሮች ስለተዘጉባቸው የአመፅን ጎዳና እንዲከተሉ የሚጋብዝ በር ተቀዶ ይገኛል።

ወያኔ ለሀገራችን ችግሮች በሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ መንገድ መፍትሄ ከመሻት ይልቅ፡ ችግሮቹ የበለጠ እንዲባባሱና እንዲያመረቅዙ ፡ ሰላም፡ መረጋጋትና ብሔራዊ ዕርቅ በኢትዮጵያ ምድር እንዳይሰፍን፡ በህዝብ መካከል የጥላቻ ሙሹ እየደረደሩ፡ የጦርነት ከበሮን ጠዋት ማታ ሲደልቁ ይታያል።

በሌላ በኩል ደግሞ በሀገሪቱ ውስጥ የፖለቲካ መረጋጋት እንዲፈጠር፡ ሕዝቡም አስተማማኝ ሰላምና ፀጥታ አግኝቶ ያለስጋት ለመኖር እንዲችል፡ የዳኝነት ተቋሞች ነፃ ሆነው የሚሠሩበት፡ የህግ የበላይነት የተረጋገጠበት ሁኔታ እንዲፈጠርና፡ ህዝቡም በህግና ሥርዓት መኖር ላይ እምነት እንዲያድርበት ለማድረግ እንዲቻል፡ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚታገሉ ኢትዮጵያዊ ተቃዋሚ ኃይሎች በተናጠልም ሆነ በኅብረት በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል። ሆኖም እስከዛሬ የተደረጉት ጥረቶችን ሁሉ በማምከን ወያኔ የሰላምና የዕርቅ መሰናከል ከመሆኑም ባሻገር በንፁሃን ዜጎች ደም ሰላምን አጠልሽቶታል። ወያኔ ስለ ሰላምና ዕርቅ ሊሰማም ሊነጋገርም እማይችልበት የደም ስካር ላይ ደርሷል።

16 ዓመት ወያኔን ካየነው በኋላ፡ የሕዝብ ደም ፈሶ፡ ብዙሃን በየእስር ቤቱ እየተሰቃዩ፡ ሕዝብ በረሃብና በበሽታ እየተሰቃየ፡ ወያኔና ጀሌዎቹ ሲፈነድቁ፡ አስረሽ ምቺው ሊሉብን እየተዘጋጁ፡ የጠጡትን ደም በሚሊኒየም ውስኪ ሊያወራርዱ ሲራወጡ፡ ዳንኪራ ሲመቱብን እያየንና እያስተዋልን፡ የወያኔ አገዛዝ የሕዝብ ዋነኛ ጠላት መሆኑን ላለመቀበል የሚደረገው ሙከራ አሁንም እየታየ ነው። <u>ትግል አቅጣጫውን እንዳያጣ፡ እንዳይስት፡ እንዳይዛባ ከተፈለገ የወያኔን አገዛዝ በሕዝብና በሀገር ጠላትነት መፈረጅ መሰረታዊ ነው።</u>

ወያኔ በታማኝ ተቃዋሚነት አሰባስቦ ይጫወት የነበረውን ድራማ ለመድገም እቅዱ ያለን፡ በሚለንየም ስም የመለስን ትከሻ ለማቀፍ ሀሳቡ ያለን ከሕዝብ ሳንጣላ፡ ወደ ማጡ ሳንገባ በፊት ድጡ ላይ ሆነን እናስብ። ሕዝብ አንቅሮ የተፋውን ወያኔ በሕዝብ ስም ሊያቅፍለት የሚጥር፡ የመለስን መላጣ ሊያሻሽለት የሚቋምጥ ግለሰብም ሆነ ድርጅት ሌላው ቢቀር ከቅርቡ የሁለት

ዓመት የትግል ታሪክ አልተማሩምና፣ በድጋሚ ከወያኔ ሽንጐ ዘው ብለው የገቡት ከሀዲዎች ዛሬ እምን ላይ እንዳሉ ሊገነዘቡ ይገባል።

በቅድሚያ ወያኔን በጠላትነት ስንፈርጅ ነው ልንታገል የምንችለው። ይህን ደግሞ እስከ ዛሬ ያልተረዳ የፖለቲካ ሀሁ ተዛብቶበታልና ትግሉን ለባለቤቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይተውለት። ወያኔ እንደበፊቱ አሁንም የማይፈልጋቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች ለመግፋት፣ ለመወንጀል፣ ለማራቅ የሚደረግ እንቅስቃሴ፣ ከወያኔ ቢያስማማም ከሕዝብ ግን አያስታርቅም። የሕዝብን የድምጼ ይከበር ጥያቄ አይመልስም። የሰሞኑ የሰላምና ብሔራዊ ዕርቅ የወሬ ነፈሳ ልናስብበትና ልንጠነቀቅበት ይገባናል። ዕርቁ ከማን ጋር ነው? የሚታረቀው ማን ነው? የዕርቁ ዓላማ ምንድ ነው? ዕርቁ የሕዝቡን ጥያቄ ይመልሳል ወይ? ወዘተ. መታየት ያለበት ጉዳይ ነው።

ከወያኔ ፀብ ያላቸውን ግለሰቦችና የፖለቲካ ድርጅቶች አስማምቶ፣ አስታርቆ ሁኔታዎች ከግንቦት 97 በፊት እነበሩበት ለመመለስ ከሆነ የትግሉ አካሄድ ሁለት እርምጃ ሳይሆን ሁለት ማይል ወደ ኋላ የማፈትለክ ያህል ነው።

ዕርቅ ስንል ሕዝብ ነው መታረቅ ያለበት። ሕዝብ ደግሞ በወያኔ አገዛዝ ሀገሩን አጥቷል። አንጡራ ንብረቱ ተዘርፏል፣ እየተዘረፈም ነው። የሀገሩ ባህልና ታሪክ፣ ማንነቱ እየተበረዘና እየጠፋ ነው። አርማው ጨርቅ ተብሏል፣ ተረግጧል። ልጆቹ ተሰደዋል፣ ታስረዋል፣ ተገድለዋል። በረሃብና በበሽታ አገዛዙ እያሰቃየው ነው። ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲበዘበዝ፤ እየተራበ፣ እየተጠማ እንዲያገሳ፤ እያለቀሰ፣ እያነባ እንዲስቅ፤ ልጆቹን አጥቶ፣ ቀብሮ ሚሊኒየም እንዲጨፍር፤ እያላገጠበት ከአለው አገዛዝ ጋር የሞት የሽረት ትግል ላይ ነው ያለው። ሀገሩን ለማዳን፣ አንጡራ ሀብቱን ለመጠበቅ፣ ነፃነቱን ለማስከበር ወያኔን በጠላትነት ፈርጆ እየታገለ ነው። በወያኔ አገዛዝ የተገደሉ ወገኖች ደማቸው ደመ ከልብ እንዳይሆን ገዳዮችንና ደም አፍሳሾችን ሊፋረዳቸው ይፈልጋል። ወያኔ የት እንዳደረሳቸው ደብዛቸው የጠፋውን አለኝታዎቹን ለማግኘት ወያኔን መቅበር ይፈልጋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የሀገሩ፣ የታሪኩ የልጆቹ የራሱ ደመኛ፣ ወያኔ መሆኑን በተግባር ያየውና እያየው ያለውን ግፍና መከራውን ከቀመሰውና እየቀመሰ ካለው ሕዝብ በላይ ስለወያኔ ማንነትና ምንነት ሌላ መስካሪ አይሻም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን በጠላትነት ሲፈርጅ ሁሌም ትግል ፈልጐ አይደለም። ሀገሩን እያደሙና እያቆሰሉ ያሉትን ተጠያቂዎችን ይፈልጋልና ነው። የኢትዮጵያን ሕዝብ እየገደሉትና እያሰቃዩት በተቃራኒው መሃሪ ነው፣ ይቅር ባይ ነው እያሉ ለሚያሾፉበትና ለሚያፌዙበት ምህረቱን በመቃብራቸው ላይ ሊያሳያቸው ይፈልጋልና ነው። ሀገርና ሕዝብን ለማዳን፣ መብትና ነጻነቱን ለመቀዳጀት እየከፈለ ላለው መስዋዕትነት የወያኔን ሞት ይፈልጋልና ነው። ወያኔን አክ እንትፍ ብሎ ሲተፋው ልምምጡንም፣ የሰላም አማራጩንም ትዕግስቱን ሁሉ አሟጦ ነው።

በተደጋጋሚ የወያኔ አገዛዝ ለሰላምና ዕርቅ ጉባዔ ተጋብዞም እምቢ ያለ ኃይል በመሆኑና ወሰን አልፎ በንፁህ ዜጋ ሕይወት ላይ ግፍ የፈፀመ ኃይል በመሆኑ ሰልፉ በጠላትነት እንጂ ለዕርቅ ሊሰለፍ በሚችል ኃይል ደረጃ አይደለም። ዛሬ ለተደጋጋሚና ለሰለቸ የወያኔ ትርይት፣ የመለስ ቅጥ ያጣ ድንፋታ፣ ለመለስ የውሸት ቱልቱላ፣ ግቡንና ዒላማውን ላላነጣጠረ ሰላምና ዕርቅ ሲወራ፣ ተባለ እንዴ፣ ባዩ ሕዝብ እንደሆነ ከወዲሁ ግንዛቤ ማግኘት ግድ ይላል። ሰላምና ብሔራዊ ዕርቅ አጥፊዎችን፣ ደም አፍሳሾችን፣ የሀገር ሀብት ዘራፊዎችን፣ ሀገርን ለባዕዳን ሸጠው የሚያስበዘብዙትን ለተጠያቂነት ማቅረብን ይጠይቃል። ተጠያቂዎቹም መለስና አገዛዙ እንደሆኑ ብዥታ ሊኖርና ልንጠራጠር አይገባንም። ከወያኔ አገዛዝ ጋር ድርድር ከተባለ ስልጣን የሚለቅበትን መንገድ እንጂ ስልጣን ተካፋይ የሚሆንበት አይሆንም። ወያኔ ከስህተቱ ተምሮና ሕዝብን ይቅርታ ጠይቆ ይጨምታል፣ ይሻሻላል፣ የሚባልበት ጊዜ አልፏል። ዛሬ ባለው ተጨባጭ

የትግል ሰልፍ ወያኔ ከሕዝብ ጋር በሞት ሽረት ትንቅንቅ የገባበት ነውና የዚህን ትግል አሸናፊነት ለማረጋገጥ ከመዋደቅ ፈንታ ለወያኔ ጊዜን የሚለግስ፡ ለወያኔ ለተደጋገመ ሹፈት የእንደራደር ጥሪ ቦታ ሊሰጠው አይገባም። የትግልን መራራነት ተረድቶ፡ የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ ሳንሰለችና ሳናወላውል ቆርጠ መታገልን ይጠይቃል።

ሰላምና ብሔራዊ ዕርቅ ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች አካቶ የሚካሄድ፡ በወያኔ መቃብር ላይ የሚያብብ ከሆነ ዕቅዳችን ለዚህ መሳካት ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በመካከላቸው ያለው ልዩነት እንደተጠበቀ፡ እስከዛሬ የተወዛገቡባቸውን አለመግባባት ለሀገር ሲሉ አርግበውና የሲቪክ ማህበራትን፡ ታዋቂ ግለሰቦችን፡ የሃይማኖት አባቶችን፡ ምሁራንን አካተው ለሚፈጠረው የመግባባት መድረክ ተዘጋጅተን በጋራ ዋናውን የሀገሪቷንና የሕዝብ ጠላትን እንታገለው ዘንድ የሚደረግ ጥረት መሆን ይኖርበታል። ይህ ሲሆን ነው በሀገራችን ላይ የተደቀነውንና ያንዣበበውን የመበታተን ወያኔ ሰራሽ አደጋ ልንገታው የምንችለው። ትግሉንም በድል አድራጊነት የምንወጣው። መከታና ኃይላችን የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከሆነ ድረስ በወያኔ አጋዚ ሳንደናገጥ፡ በወያኔ ጥይት ሳንፈረጥጥ፡ ለሚጠበቅብን የጋራ ትግል በጋራ እንሰለፍ።

የተቃዋሚ ኃይሎች የራሳችንን መለስተኛ ችግሮች እስካልፈታንና ለጋራ ትግል በጋራ ለመሰለፍ ካልጣርን ሁሌ ወያኔንና ባዕዳን ኃይሎችን ብቻ እያመካኘን፡ የችግራችን ምንጭ እያደረግን ብንለፍፍ ጥንካሬያችንን ልናጎለብት አንችልም። በሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥም ከራስ ጋር ያለመታረቅ ችግር ያለ መሆኑን አምነን፡ ተቀብለን ለመሠረታዊ የሀገር ደህንነት ስንል እራስን እየመረመሩና እየገመገሙ፡ ስህተትን አርሞ፡ ከስህተትም እየተማሩ ከራስና ከሌላው ጋር ታርቆ የጋራ ሀገርን በጋራ የማዳንና የመገንባት ርምጃ ካልጀመሩ፡ የኛ መከፋፈልና የየብቻ ጉዞ ወያኔን እየተንገዳገደም ቢሆን እንዲቆይ፡ እንዲጠናከር ከማድረግ ባሻገር ሌላ ጠቀሜታ የለውም።

እንደ ኢትዮጵያ ባለብዙ ፈርጅና የተወሳሰበ ችግር ያላትን ሀገር ለማስተዳደር፡ ምን ያህል አስቸጋሪ መሆኑን ያልተረዳ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪ፡ እራሱን ደጋግሞ መመርመር ይኖርበታል። ነገ ተነገ ውዲያ ኢትዮጵያን እመራለሁ ብሎ የሚያስብ የፖለቲካ ድርጅት፡ ከአሁኑ፡ ከራሱ ጋር እየታረቀ፡ ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር እየተስማማና ሕዝባዊ ዓላማን አስቀድሞ አስፈላጊውን የጋራ መሰናዶ ማድረግ ካልቻለ፡ በኋላ “ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ” ቢባል መፍትሄ አያመጣም።

ኢትዮጵያን ለማዳን ዛሬ ሁሉም ዜጋ ሀገራዊ ግዴታ አለበት። ትግሉ ይበልጥ መፋፋም፡ ይበልጥ መጨስ፡ መጋጋም፡ መንደድ ይጠበቅበታል። ትግሉን ለማፈንና አቅጣጫውን ለማሳት የወያኔ መንጋ እየተሯሯጠ ነው። በውጭ ያለውንም የሕዝብና የድርጅቶችን ተቃውሞ ቢቻለው ለማዳፈን፡ ካልሆነለት ደግሞ ለማዳከም፡ በአሁኑ ወቅት የወያኔ ከፋፋይ ቡድን በየቦታው በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ እያየን ነው። ይህ ቡድንም፡ ምሁር ነን፡ አስታራቂ ነን፡ ሽማግሌ ነን ወይም ታጋይ ነን በሚሉ መሰሪዎችም እየተደገፈ ነው። የሕዝብ ክንድ ይላላ፡ ይደክም ዘንድ፡ በከፋፋይ ሴራ የተሰማሩትን ነቅቶ መጠበቅ፡ ትግሉን መከላከል ብቻ ሳይሆን ወያኔ ለባሾችን፡ ሰላዮችን ሳንፈራ እየመነጠርን ማጋለጥ ይኖርብናል። ዘረኛው ቡድንና ጭፍሮቹ የሕዝቡን ትግል ለመከፋፈል ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እየጣሩ ናቸውና። ሕዝብ አንድነቱን ጠብቆ፡ ኢትዮጵያዊነቱን አስከብሮ የወያኔን ቡድን ለአንዴም ለሁሌም ለማስወገድ አስፈላጊውን መስዋዕትነት እየከፈለ ባለበት ወቅት የፖለቲካ ድርጅቶችን እገዛና አመራር ይጠይቃል። የሕዝብ አሸናፊነት አጠራጣሪ ባይሆንም፡ አሸናፊ ለመሆን ግን መታገል መቅደም እንዳለበት ምን ጊዜም መረሳት የለበትም። ለዚህ መሠረቱ ግን ከራስ ጋር እየታረቁ፡ ከወገን ጋር እየተስማሙ በጋራ ዓላማና ብሔራዊ አጀንዳ ዙሪያ ተሰባስቦ በጋራ መታገል ብቻ ነው።

የትግል ዓላማዎቻችንን በሚገባ አውቀንና ተረድተን፣ ወዳጅና ጠላትን በየፈርጁ ለይተን መጓዝ፣ ለመፍትሔ ፍለጋው ጥረት በብርቱ ይረዳናል። ለዚህ ጥረት ስኬታማነት ኃላፊነቱና ተጠያቂነቱ የሚያርፈው በቅድሚያ በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሀገሪቱ ምሁራን ላይ ነው። ሀገሪቱ አሁን ከገባችበት የጥፋት አዘቅት ለማውጣት እነኚህ ሁለት የኅብረተሰብ ክፍሎች ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ሊያውቁት ይገባል።

በተረትነቱ እንቀበለውና "ልጅ ያቦካው..." ተለውጦ "አዋቂ ያቦካው..." ካልሆነ በስተቀር፣ ኢትዮጵያን አሁን ካለችበት ችግር ለማዳን ብቻ ሳይሆን፣ ከወያኔ ዘረኛ ሥርዓት በኋላ ለሚከሰተው በሀገሪቱ የፖለቲካ መልከአምድር ላይ ወሳኝና ገንቢ ሚና አላቸው። ትግል ታጋይ ድርጅትና የምሁራንን ተሳትፎ ይጠይቃልና እነኚህ ክፍሎች ሊተባበሩና በጋራ ብሔራዊ አጀንዳ ዙሪያ አብረው ሊሰሩ የግድ ይላል።

ለመሆኑ በአሁኑ ወቅት የሀገራችንና የሕዝባችን የቅድሚያ አጀንዳ ምንድን ነው? የምንፈልገውን አውቀን በቅደም ተከተል ተራ አስገብተን ልናራምደው የሚገባን ሀገራዊ የትግል ሂደት እንዴት ማከናወን ይገባናል? ልናነጣጥርበት የሚገባን የጋራ ዒላማችን በማን ላይ ነው? በርግጥ የተቃዋሚ ኃይሎች በጋራ የሚያነጣጥሩበት የጋራ ዒላማ አላቸውን? ወይስ ዒላማቸውን የሚያነጣጥሩት እርስ በዕርሳቸው ላይ ነው? ኸረ ለመሆኑ ሁሉን ያላሳተፈና ያላስተባበረ ትግል፣ ውጤት ያስገኛል ብለው ያምናሉ? ይህን አምባገነን ዘረኛ ሥርዓት በአጭር ጊዜ ለመለወጥ የሚቻለውስ እንዴት ነው? እነኚህንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እየጠየቁ ትክክለኛ መልሶችን አግኝቶ በተግባር መለወጥ መቻል ማለት፣ የምንፈልገውን አውቀን የቅድሚያ ተግባራችንን ተረድተን ወደ ሥራ ለመተርጎም ተዘጋጅተናል ማለት ነው። ይህ ከሆነ ዘንዳ፣ ሁሉንም ለማሳተፍና ለማስተባበር የተሟላ ሁኔታን ፈጥረናል ማለት ነው። እናም ደግሞ፣ ሁሉም የሚመኘው የተቃዋሚ ድርጅቶችና የኢትዮጵያ ምሁራን ብሎም መላው ኅብረተሰብ የተባበረበት ትግል ይካሄዳል ማለት ነው። ይህን ማሳካት ከቻልን ደግሞ በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤት ለማስመዝገብ የሚሳን አይሆንም።

ትግሉን ከግቡ ለማድረስ የተቃዋሚ ኃይሎች ህብረት አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደለም። ይህ የመሰባበብ እርምጃ ግን መለስተኛ ስምምነት ያሸዋል። <u>በኅብረቱ የሚካተቱ ኃይሎች በኢትዮጵያ ለኢትዮጵያ የሚታገሉ ናቸው። ኢትዮጵያዊ አይደለንም፣ ባዕዳን ነን፣ ትግላችን ወደፊት ከኢትዮጵያ ጋር በጉርብትና ለመኖር ነው ወዘተ. የሚሉ ኃይሎች ካሉ በዚህ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች ኅብረት ሊሰባሰቡ የሚፈልጉም የሚችሉም አይሆኑም።</u> በዚህ መሠረታዊ ሀሳብ ላይ ግልፅ የሆኑ ኃይሎች መተባበር አለባቸው። ኅብረቱ ከወያኔ ለመደራደር ሳይሆን የሕዝብ ትግል መርቶ ከግብ ለማድረስ ነው። ወያኔን ለማስወገድ ነው!!!

ሀገርን ከአደጋ ለማዳን በጋራ መታገል!
ወያኔ የሀገርና ሕዝብ ጠላት ነው!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!